ቀን፣ 26.09.2016 ዓ.ም.ፈ

## ከአቶ ግደይ ዘርአጽዮን ጋር የተደረገ ቃለምልልስ

የትዴት የህዝብ ግኑኝነት ክፍል አቶ ግደይን አሁን በኢትዮጵያ ባለው ሁኔታ ላይ ሃሳባቸውን እንዲያካፍሉን የሚከተለውን በጥያቄና መልስ መልክ አቅርበንላቸዋል።

አቶ ግደይ ዘርአጽዮን ከህወሓት መስራቾች አንዱና ከድርጅቱ በ1977ዓም ለቀው የወጡ በተቃዋሚነት የትዴት አባል በመሆን እየታገሉ ያሉ ናቸው።

ጥያቄ፣

በኦሮሞ ለዘጠኝ ወር ያህል አሁን ደግሞ በአማራ ክልል፣ በኮንሶ፣ ሲዳማ፣ ጋምቤላ እንዲሁም በትግራይ በተምቤን ዓብይ ዓዲ፣ አጽቢ፣ መቐለ፣ ነበለት እና በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች እየተካሄዱ ያሉትን ህዝባዊ ተቃውሞዎችና አመጾች እንዴት ያዩታል?

ግደይ፣

የህወሓት/ኢህአደግ ጨቋኝ ስርዓት በመገንዘብ ይህ ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል ከዓመታት በፊት ቀደም ብለን ስንተነብየው የቆየ ነው። ማዕበሉን የቀሰቀሱት በኦሮሞ የአዲስ አበባ ከተማን የማስፋት ፕላን በአማራ ደግሞ የወልቃይት የማንነት ጥያቄ ቢሆንም ሁሉም በጋራ የሚያነሱት ቅሬታና ተቃውሞ ለ25 ኣመታት ህወሓት/ኢህአደግ በህዝቡ ያደረሰው ጭቆና፣ የዲሞክራሲና ፍትህ እጦት፣ የዘር አድልዎ፣ ሙስና፣ የወጣቱ ስራ ማጣት፣ የኑሮ ውድነትና ድህነት ህዝቡ ከሚሸከመው በላይ ስለሆነበት መሆኑን ነው። ህወሓት እንቅስቃሴውን ሰራዊቱን በመጠቀም ህዝቡን በመግደልና በማሰር በኃይል ሊያዳክመው ቢሞክርም ህዝቡ ለርዥም ጊዜ ተቃውሞውን በመቀጠል ላይ በመሆኑ በታሪካችን አዲስና አኩሪ ሂደት እና የነጻነት ተስፍም መሆኑ ይታየኛል።

ጥያቄ፣

እንቅስቃሴው በስሜት የተነሳሳና የተቀናጀ አመራር የለውም ስለሆነም ያለው ስርዓት ሂደቱን ሊቀጨው ይችላል በህዝብም ብዙ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል የሚል ስጋት አለ ይህንን እንዴት ያዩታል?

ግደይ፣

እርግጥ ህዝቡ ጭቆናውን ሊሸከመው ከሚችለው በላይ ስለሆነ በስሜትና በድንገት የተነሳሳ ነው። የህዝቡ መነሳሳት የፖለቲካ ድርጅቶችና ተቆርቋሪ ምሁሮች፣ ጋዜጠኞች ህብረተሰቡም ጭምር ለረዥም ጊዜ እየተመቱና እየተነሱ ያበረከቱት የትግል ውጤት ቢሆንም አሁን ባለበት ሁኔታ ግን ፖለቲካዊ ድርጅቶች እየመሩትና እያቀናጁት አለመሆኑ ግልጽ ነው። አገር ቤት ያሉት ድርጅቶች ስርዓቱ በተደጋጋሚ እያጠቃቸው እንዲዳከሙ በማድረጉ ሲሆን ውጭ ያሉት ደግሞ በተለያዩ ጥቃቅን ልዩነቶች ራሳቸውን ሳያዘጋጁ በመቆየታቸው መሆኑ ግልጽ ሆኗል። ትዴት ይህ ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል ቀደም ብሎ በመገንዘብ ተመሳሳይ አመለካከት ካላቸው ከሌሎች ፖለቲካና ሲቪክ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ የትግል ሸንጎ (ሸንጎ) በሚል ስም ከአራት ዓመት በፊት በማቋቋም ሰፊ ስብሰብ እንዲደረግ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል መሆን ካለበት ደረጃ ላይ ግን አልደረሰም። አሁንም 'ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ` ቢሆንም አገር ቤት ያሉትም በውጭ ያሉትም ትግላቸውን ማስተባበር ግድ ይልባቸዋል። የተቀናጀ ፖለቲካዊ አመራር የሌለው ህዝባዊ አምጽ በቀላሉ ሊመታ ይችላል ቢያሸንፍም ውጤቱ የምንፈልገውን ዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ እንዲሁም የተባበረች ኢትዮጵያ ላይሆን ይችላል።

ጥያቄ፣

በአማራና በኦሮሞ እንቅስቃሴዎች የአጋርነት ሂደት መታየቱ መልካም ቢሆንም በአማራ እንቅስቃሴ የሚታየው ግን በትግራዮች ላይ ጥላቻና ጥቃትን ተገንዝበናል ይህንን እንዴት ያዩታል?

ግደይ፣

የአማራው ህዝብ አማራ በመሆኑ ብቻ በህወሓት ብዙ ግፍ ደርሶበታል። ህወሓት/ኢህአደግ ስልጣን ሲይዝ ጀምሮ አማራው በተለያዩ ቦታዎች ሲገደልና ሲባረር አልተከላከለለትም ብቻ ሳይሆን የጥቃት ጀማሪ/ሎኻሽ ተባባሪም በመሆን ጭምር ነው። ህወሓት ስልጣን ከያዘም በኋላ አማራ እንደ ጠላት ፈርጆ የሚሄድ ድርጅት ነው። የህወሓት መሪዎች በስልጣን ለመቆየት ህዝቦችን በዘርና በሃይማኖት እርስ በርስ በማጋጨት ሲጠቀሙበት ቆይቷል። በኦሮሞ ክልል አማራ የኦሮሞን ሴት ጡት እየቆረጠ የሚያሳይ ሃወልት እንዲተከል የፈቀደ መንግስት ነው። አማራ በቅርቡ በአስር ሺዎች ከጉራፈርዳ፣ ከቤነሻንጉል ሲፈናቀሉ መንግስት እያየውና እየፈቀደም ነው። ከዛም አልፎ ለተፈናቀሉት መጠለያና ምግብ ማቅረብ ሲገባው ኣላደረገም ህዝቡ በየካባቢው ወድቋል። ይህን የመሳሰሉ ሁኔታዎች ትልቅ ጥላቻና ምሬትን ቢፈጥሩ የማይጠበቅ አይደለም። እዚህ ላይ የምለው ግን ይህ በደል የሚፈጽሙት የትግራይ ገዢው መደብ የህወሓት መሪዎች እንጂ የትግራይ ህዝብ አለመሆኑን የአማራው ህዝብ ሌላውም የኢትዮጵያ ህዝብ ግንዛቤ እንዲያደርግ ነው። የትግራይ ህዝብ እንደሌላው ህዝብ የተጨቆነና የተከፋ ህዝብ ነው። ህወሓት ህዝብ ከህዝብ ጋር እንዲጣላ ፍላጎቱ ነው። ቅራኔው ከሚገባው በላይ እንዲባባስና ጎልቶ እንዲታይ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል። የኣባይ ጸሃየ እና የስዩም መስፍን ስለጀኖሳይድ በቅርቡ ያደረጉት ቃለ መጠይቅ ይኸው ከፋፋይ ዘዴያቸው ነው። የትግራይ ህዝብ ፈርቶ ከነሱ ጋር እንዲጠጋና በትግራዋይ ስም በሌላው ህዝብ ላይ ጭፍጨፋ ለመፈጸም እንዲመቻቸው ነው። ሁሉም ለዲሞክራሲና ለኢትዮጵያ አንድነት የሚታገል ኃይል ወደ ህወሓት ወጥመድ እንዳይጠለፍ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት እላለሁ። በአንዳንድ አካባቢዎች በትግራዎች ላይ ያነጣጠረ ጥቃትና ፕሮፖጋንዳ አግባብ ያለው አይደለም ታጋዩ ኃይልም ቶሎ ማረም ይገባዋል።

ጥያቄ፣

አቶ ገርመድህንና ሌሎችም ወልቃይትን በሚመለከት እርስዎና ዶክተር አረጋዊ በነበራቹሁበት ጊዜ ነው ወደ ትግራይ እንዲገባ ያደረጋቹህት ስለሆነም አሁን ለተፈጠረው ችግር ተጠያቂዎች ናቹህ የሚል አለ ለዚሁ ምን መልስ አለዎት?

ግደይ፣

ትግሉን ስንጀምር ትግራይ የሚባለው ያኔ የትግራይ ጠቅላይ ግዛት የነበረውና ከአለወሃ መለስ እና ወልቃይት ያለው ትግሪኛ ተናጋሪ የሚኖርበትን ያጠቃለለ መሆኑን ነበር። ወልቃይት በትግራይ ክፍለሃገር አልነበረም። ወልቃይት ስንገባ መጀምሪያ ከኢድኅ ቀጥሎ ከኢህፓ ከዚያም ከደርግ ሰራዊትና ነጭለባሽ ጋር በመዋጋት ነው። ህዝቡ ግን ከኛ ጋር አልተዋጋም። ሌላውም የትግራይ አካባቢ በዚሁ መልክ ነው የተቆጣጠርነው። ወልቃይት መነሃርያ (ቤዝ) ነበረን ህዝቡ አማራ ነኝ ወይም ጎንደሬ ነኝ ብሎ ተቃውሞ ያሳየበት ሁኔታ አልነበረም። አማራ ክልል'ኮ ህወሓት ስልጣን ከመጣ በኋላ የፈጠረው ነው ከዛ በፊት አማራ የሚባል ክልል አልነበረም። ወልቃይት በትግራይ ካርታ ባናስቀምጠውም ኖሮ በወታደራዊ ስትርተጂ አስፈላጊነቱና ለውጭ መወጣጫ ተፈላጊነቱ አካባቢውን መቆጣጠር የግድ ይል ነበር። በተመሳሳይ መንገድ ህወሓት አዲስ አበባ እስኪደርስ የአማራ፣ የጋንቤላ፣የኦሮሞ ወዘተ. ቦታዎችን እየተቆጣጠረ ነው የገባው። ህወሓት ስልጣን ከያዘ በኋላ ክልሎች ሲፈጠሩ ወልቃይትና ጸገዴን ትግራይ ውስጥ አስገብቶ ዓፋርንና አገውን አስወጥቷል። በዛን ጊዜ ከወልቃይትም ከጸገዴም ተቃውሞ መኖሩን አልሰማሁም። አሁን ምን ቀሰቀሰው የሚለውን ትተን ለዚህ መልስ ምን መሆን አለበት የሚለውን ለማየት ብናተኩር መልካም ይመስለኛል። በበኩሌ ክልሎች በቋንቋ ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚያዊና

ጅዮግራፊያዊ፣ ማህበራዊ ግልጋሎትና አቅርቦት፣ አስተዳደር ወዘተ የመሳሰሉትን መመዘኛዎች በመጨመር ቢካለሉ የተሻለ መቀራረብንና ዕድገትን እንዲሁም ሰላምን ይፈጥራል የሚል እምነት አለኝ። ስለሆነም አንድ አገር ውስጥ እስከሆነ ድረስ ወልቃይት ትግራይ ሆነ ወይም አማራ ክልል ምንም ለውጥ የለውም። ባለፉት 25 ዓመት ኢትዮጵያ የብሄሮችን ጥያቄ በሚመለከት የሙከራ አገር ሆና ቆይታለች። የተለያዩ ሙከራዎች ተደርገዋል። በቋንቃ የተከለሉ አሉ፣ እንደ ደቡብ ኢትዮጵያ ደግሞ የተለያዩ ቋንቋዎችና ባህሎች ያላቸው ባንድ ክልል የሆኑ አሉ፣ ስልጤ ጉራጌ አይደለሁም ስላሉ የስልጤ ክልል ተፈጥሯል ግን አሁንም በደቡብ ህዞቦች ክልል ውስጥ አሉ፣ ከትግራይ ዓፈር ወደ ዓፋር አገው ደግሞ ወደ አገው ክልሎች የሄዱበት ሁኔታ አለ። ያለውን ስርዕትና ህገደንብ ከተቀበልን የወልቃይት ክልል በነዚሁ ፎርሙላ መንገድ ሊፈታ ይችላል ማለት ነው። የማንነት ጥያቄ ግን የተለየ ነው ህዝብ ራሱ መወሰን አለበት። አንድ ህዝብ ማንነቱን የሚገልጸው ራሱ ነው። ትግርኛ እየተናገረ አማራ ነኝ ካለ መብቱ ነው በአንጻሩም አማርኛ ተናጋሪ ሆኖ ትግሬ ነኝ ካለ መብቱ ነው። ስለዚህ ህዝቡ ማንነቱን ለመወሰን ሪፈረንደም ያድርግ ነው የምለው። ስርዓቱ ሪፈረንደሙን በትክክል ሊያካሂድ ይችላል ወይ ለሚለው በበኩሌ እምነት የለኝም ህዝቡም እምነት የለውም። ዲሞክራሲ በሌለበት ስርዓት ነጻ ሪፈረንደምና ምርጫ ሊደረግ አይችልም የብሄሮች እኩልነትም አይጠበቅም። ህወሓት/ኢህአደግ የወልቃይት ሽማግሌዎችንም ያሰረው የህዝብን ድምጽ ስለማይሰማ ነው። ከዚሁም በመነሳት ነው ሁሉም ኢትዮጵያኖች በጋራ ለዲሞክራሲና ለፍትህ ለሚደረገው ትግል ትኩረትና ቅድሚያ በመስጠት በጋራ እንታገል የምንለው።

በዚህ ላይ ገብረመድህንን ስላነሳህ እሱ እየነዛው ያለውን ውሸትና እኩይ ስራ ላይ ትንሽ ልናገር። ገብረመድህን ስለ 06 በኢሳት ሲጠየቅ ሰምታችሁት ከሆነ ስለኔ መጥፎ እንዳልተናገረ ታስታውሳላቹህ። በመጀመሪያ ይህ ሰው ብዙ ዓመት የታገለ እንጂ መስራች አይደለም። በ1978ዓም ገደማ ድርጅቱን ጥሎ ከአብራሃም ያየ ጋር ወደ ደርግ እንደገባ አብዛኞቻችን እናስታውሳለን። ያኔ አብራሃም ያየ የሆነውንና ያልሆነውን ሲዋሽና የህዝቦችን ግኑኝነት የሚያሻክር መርዛም ውሸት ሲዋሽ ገብረመድህን ምንም አይናገርም ነበር። በወቅቱ ‘ውሸት ሲደጋገም ሓቅ ይመስላል’ በሚል ያወጣሁት ጽሁፍ ላይ አብራሃም ያየ ታጋይ እንዳልነበረና እየዋሸ መሆኑን ስገልጽ ሰው አላዳመጠኝም እንዲያውም ብዙዎች ተሳልቀውብኛል። ያኔ ‘ንጹህ ኢትዮጵያዊ አብራሃም ያየ ነው እንዲያውም ትንቢት ነጋሪ’ ሲባል ነበር። ሌባ ለአመሉ ዳቦ ይልሳል እንዲሉ ትንሽ ቆይቶ ሲያወግዘው ከነበረው ሻዕብያ ጋር ዘው ብሎ ገባ። ኢትዮጵያን መውቀስ ጀመረ። ከዛም ወጥቶ ሲሰድባቸውና ሲያጠቁራቸው ከነበሩት መለስና ህወሓት ዘው ብሎ ገባ ተቃዋሚውን ማጥቆር ጀመረ በመጨርሻ በህዝብ ተተፋ። አሁን ድምጹም አይሰማም። አብራሃም ያየ ለኔ ባለውለታየ ነው። በ1978ዓም. ሱዳን ውስጥ ህወሓትን በመቃወም ሳወጣቸው የነበሩትን ጽሁፎች ለህዝብ ይበትንልኝ ነበር። ይሁን እንጂ ጭፍን ውሸቶችን ሲናገርና ህዝብን ከህዝብ የሚያጋጭ ሲሆን ዝም ብየ ለማየት ኅሊናየ አልፈቀደልኝም። እንደዚሁም አሁን በገረመድህን ላይ። በትግል ወቅት ህወሓት አማራን ስለሚጠላ በአማራዎች ላይ ብዙ እስራትና ግፍ እንደፈጸመ አድርጎ ለማሳየት፣ የትግራይ ህዝብም አማራን ይጠላል በማለት አስጸያፊ ስድቦችን ጭምር ይናገራል። እንኳን ሳይደረግ ቢደረግም አስጸያፊ ስድቦችን እሱም ሆነ አስተናጋጁ ኢሳት በሚድያ ማቅረቡ ምን ጥቅም ሊያስገኝ እንድሚችል አይገባኝም። ትግራይ ውስጥ በነበረው ትግል አማራ በብዛት የሚታሰርበት ሁኔታ አልነበረም። ለመሆኑ የት የነበረው አማራ ነው የሚታሰረው? ምርኮኞች ቢሆኑም ሁሉም ያለ አድልዎ ከአንድ ወር ላልበለጠ ለትምህርት ቆይተው የሚለቀቁበት ሁኔታ ነው የነበረው። ለምርኮኞች እስር ቤትም አልነበረም ከባህል ጋር በየገጠሩ እይዞሩ ምርኮኞችም የየክልላቸውን ባህል የሚያስዩበት ሁኔታ ነበር። እውነቱን የፈለገ ተማርከው ከነበሩት የአማራ ተወላጆች ጠይቆ ሊያገኝ ይችላል። ከዚሁም በላይ የህወሓት ታጋይ በአማራው ክልል አልፎ ነው አዲስ አበባ ድረስ የገባው። ሰራዊቱ ህዝቡ ምግብ ካልሰጠው ተርቦ የሚተኛ፣ ቤትና ምንጣፍ ካልተሰጠው በራንዳ ወጥቶ መሬት ላይ የሚተኛ፣ ሰው አክባሪና ድስፕሊንድ መሆኑን ህዝቡ ራሱ አይቶታል። ይህን ታጋይ፣ ይህን ህዝብ ነው አማራን ይጠላል ብላችሁ ለኢትዮጵያ ህዝብ የምታቀርቡት? ገረመድህንስ የዝህ ዓይነት ውሸት ለምን ይቀምማል?

ጠያቂውም በቀላሉ ውሸቱን ለማየት የሚችልበት ሁኔታ እያለ ተቀብሎት ያልፋል። 06 ያለበት የጦር ቀጠና ስለሆነ ታጋዩም ሆነ እስረኛው በአየር እንዳይመታ የሚሰሩት ቤቶች ከመሬት በታች ናቸው ወይም ዋሻ ነው። እስር ቤቶቹ ሁለት ሜትር ከመሬት በታች መሆናቸው ምን የሚያስደንቅ ነገር አለው። እንዲሁም በጦርነት ውስጥ ስለሆነ ህጉና የፍርዱ ሁኔታ ወታደራዊ ነው። በሲቪል እና በጦር ፍርድቤቶች ልዩነት መኖርን የምንገነዘብ ይመስለኛል። በአንድ እስርቤት እስከ 3000 እስረኛ በአንድ ወረዳ 150 እስር ቤቶች እያንዳንዱ እስከ 150 እስረኛ የሚይዝ በአንድ ወረዳ ካ15,000 እስረኛ በላይ ማለት ነው። ይህንን ውሸት ለመገመት አይችልም። ህወሓት ለዚህ ሁሉ እስረኛ ስንቅስ ከየት አምጥቶ ይችለዋል። ሁሉም ውሸታሞች እንዲታመኑ ቁጥር፣ ቀን፣ የቦታና የሰው ስም ያቀርባሉ። ገብረመድህን የ06 አባል አልነበረም ይህን ሁሉ በዝርዝር ለማወቅ እንዴት ቻለ ብሎ ጥያቄ ማንሳት አይገባም? እኔ የፖሊት ቢሮ አባል ሆኜም ብዙ የማላወቀው ነገር አለ። ከዚህ ሁሉ ክስ ደግሞ እኔን (ግደይን) ነጻ ያወጣኛል። እኔ ከሌሎቹ የተለየሁ መልአክ አልነበርኩም። በዛን ወቅት ለተፈጸሙት መጥፎም በጎም ተግባር እኩል ሃላፊነት ነበረኝ። የተጋነነ አቀራረቡንና ብዛቱን ትተን ሰዎች ታስረዋል ተደብድበዋል ተገድለዋል ትክክል ነው። ማን ለምን በምን ሁኔታ የሚለውን ግን ጭብጥ ይዞ መጠየቅና በወቅቱ ከነበረው ህግና ሁኔታ አንጻር የተወሰደ እርምጃ ነው ወይስ ከህግ ውጭ የሚለውን መመርመር ያስፈልጋል። ህወሓትም ለዚህ ዓይነት ጥያቄና ምርመራ ግልጽ መሆን ይገባዋል እላለሁ። በበኩሌ እኔ በነበርኩበት ወቅት ሊደበቅ የሚገባው ነገር አለ ብየ አላምንም። ገብረመድህን የዚህን ዓይነት ውሸት በመቀመም ምን ጥቅም ያገኛል ለሚለው ለማወቅ አልቻልኩም ግማቱ እስኪ.ታይ ግን ልክ እንደ አብርሃም ያየ 'ከትግሬዎች ብቸኛ እውነታኛ ኢትዮጵያዊ' እይተባለ ነው። ለወደፊት አብረን እናያለን።

ሌላው በጣም የሚያሳዝነኝ ኢሳትና ሌሎች ሚድያዎች ህዝቡን የሚያስተባብርና ፍቅርን የሚያዳብር ዜናዎችንና ትምህርቶችን በማቅረብ ገንቢ ሚና ሊጫወቱ ሲገባቸው የዚህን ዓይነት ርካሽ ውሸት ህዝብን ከህዝብ ጋር የሚያጋጭ እየደጋገሙና እየተቀባበሉ ማስተላፋቸው ነው። አንዳንዶቹን ነገሮች እንኳን ለማረጋገጥ ውጭ ያለነውን ድርጅቱን በደንብ የምናውቀውን አልጠየቁንም ወይም ፊት ለፊት አላጋፈጡንም። እባካቹህ ለእውነት፣ ለዲሞክራሲና ሰበኣዊ መብት ቁሙ።

ጥያቄ፣

ከሳምንታት በፊት ጀነራል ጻድቃን ገብረትንሳኤ በኢትዮጵያ ባለው ሁኔታና ተቃዋሚዎችን የሚያስታፍ የሽግግር መንግስት እንድዲደረግ፣ አሁን ያለው ህገደንብ ለሽግግር ወቅት ሊያገለግል እንድሚችል ጽሁፍ አውጥቷል። ይህንን እንዴት ያዩታል?

ግደይ፣

ይህ አዲስ ሃሳብ አይደለም። ተቃዋሚ ድርጅቶችና ምሁራኖች በተደጋጋሚ ሲያቀርቡት የነበረ ሃሳብ ነው። ልዩ የሚያደርገው ህወሓት/ኢህአደግ ጥሪውን ስያጣጥለውና ሲሳለቅበት የነበረ ሲሆን አሁን በሱ በኩል ያሉ ሰዎች ሃሳቡን መቀበላቸው ነው። በዚያ ጎራ ውስጥ ይህ ሃሳብ እየተሽከረከረ መሆኑ ጥሩ ምልክት ነው፣ የሚያነሱትን ሰዎች ማበረታታት ያስፈልጋል። ያለው ህገደንብ ለሽግግር ያገለግላል በሚለው ላይ አካራካሪ ሊሆን ይችላል። ለዲምክራሲና ፍትህ መጥፋት፣ በስልጣን ለመባለግ፣ ለሙስና፣ በህዝቦች መካክል ልዩነቶችን በመፍጠር ሽፋንና መሰረት የሆነው ህገደንቡ ነው። ቢሆንም በበኩሌ ካለው ህገደንብ ጠቃሚ የሆኑትን ወስደን የማይጠቅሙንን አስወጥተን ልንሰራበት እንችላለን የሚል ኣመለካከት አለኝ።

ጥያቄ፣

ለህዝቡ የሚያስተላለፉት መልእክት አለ?

ግደይ፤ከላይ የጠቀስኩት በሙሉ ህዝቡ እንዲይዳምጠው የምፈልገውን ነው። በአሁኑ ወቅት ታጋዩ ህዝብ እና ፖለቲካዊ ድርጅቶች ኃይሉን ማስተባበርና ማቀናጀት ይጠበቅበታል ሁሉም ለዚሁ ተግባር ተግቶ መስራት አለበት። የትግራይ ህዝብና ሌላውም የኢትዮጵያ ህዝብ የህወሓት የውሸት ፕሮፖጋንዳ ሰለባ እንዳይሆንና እርስ በርስ እንዳይጋጭ ታላቅ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል። አንዱ ክልል ሲጠቃ የሌላውም ክልል ጥቃት ነው። እኔ ትግራዋይ ነኝ፣ እኔ አማራ ነኝ፣ እኔ ኦሮሞ ነኝ፣ እኔ ዓፋር ነኝ፣ እኔ ሁሉም ነኝ ወዘተ፣ ባጠቃላይ እኔ ኢትዮጵያዊ ነኝ በማለት ትግላችንን ማጠናከርና የህወሓት/ኢህአደግን ከፋፍለህ ምታ/ግዛ ሴራ ማኮላሸት አለብን እላለሁ። ሃሳቤን ለማካፈል ለተሰጠኝ እድል አመሰግናለሁ።